

**❧43-1☙**

# ጠቃሚ ምክር
# “በትዳሬ ውስጥ ሰላም አጣሁ” ለሚሉ

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሙሉ ደስታና ምቾት ይሰጡታል ብሎ ያሰባቸውን ነገሮች ሁሉ በስፋትና በብዛት አመቻችቶ ከፈጥረ በኋል መጨረሻ ላይ ሰውን ፈጠረ። ይሁን እንጂ ሰው ብቻውን በመሆኑ ደስታው የተሟላ እንዳልሆነ የተመለከተው እግዚአብሔር “ሰው ብቻውን መኖሩ መልካም አይደለም፤ ተስማሚና ረዳት ጓደኛ እፈጥረ ታለሁ” (ዘፍጥረት 2፥18) አለ። የሰው ልጅ ከእንቅልፍ ሰመመኑ ሲነቃ እግዚአብሔር አበጃጅቶና አሰማምሮ የሠራትን ሴት አምጥቶ ሲያሳየው ወደዳትና “እነሆ በመጨረሻ እኔኑ የምትመስል አገኘሁ፤ እርስዋ ከአጥንቴ የተገኘች አጥንት ናት፤ ከሥጋዬም የተገኘች ሥጋ ናት” አለ (ዘፍጥረት 2፥23)።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ከሰጠው መልካም ስጦታዎች መካከል አንደኛው “ጋብቻ” ነው። ብዙ ታላላቅ ሰዎች ጋብቻን አድንቀው ጽፈዋል፥

“ያገባ ሰው ቀፎውን እንዳበጀ ንብ ነው። አካባቢውንና ዓለምን ያሳድጋል። በትጉህ ሠራተኛንቱ ሁሉ ይጠቅማል እንጂ ማንንም አይጎዳም። ከጋብቻ ሸሽቶ የሚኖር ግን እንደ ተርብ የትም ይንከራተታል፤ አካባቢውን ያበላሻል፣ ሰላም ይነሳ፣ የኔ የሚለው ነገር ስለሌለው የሌሎችን ጣፋጭ ማር ይሠርቃል፤ ከሌሎች ቀፎ ውስጥ ለመዝረፍ ስለሚገባ በሌሎች ሕይወት መሰናከልና ችግር ይፈጥራል” ፊልተም

“መልካም ጋብቻ መሥርቶ የኖረ ሰው ሲሞት በሚወዱት ልጆቹና በምትወደው ሚስቱ ተከቦ ዕንባ ያቀረሩ ዓይኖች እያዩት ይሞታል። ሳያገባ የኖረ ወንደላጤ ግን የተፈጥሮ ሞት አይሞትም። ነገር ግን በሕይወት እያለ በስብሶ ያልቃል” አርቲመስ ዋድ

“መልካም ጋብቻ የአዲስ ሕይወት በር ነው፤ ደስታ የሞላበትና ጠቃሚ ሕይወት የሚኖርበት የሕይወት መጀመሪያ ነው” ኤ. ፒ. ስታንሊ

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ጋብቻ የሚሰጠው አስተያየት አለው። “ሚስት ካገኘህ መልካም ነገር አግኝተሃል ማለት ነው፤ ምክንያቱም ሚስት ከእግዚአብሄር የምትሰጥ በረከት ናት” ይላል (ምሳሌ 18፥22) ።

በጋብቻ ሕይወት ውስጥ አልፈው መልካም ልምምድ የሌላቸው ሰዎች “ጋብቻን” የሚያዩትና ለማሳየት የሚሞክሩት ጣፋጭነቱን ሳይሆን መራራነቱን፣ ጠቃሚነቱን ሳይሆን ጎጂነቱን ነው።

“ሰው በጋብቻው ዕድለ ቢስ ከሆነ ሲወለድ ዕድለኛ ሆኖ መወለዱ ምንም አይረባውም” ዳይስየር

“ኦ ጋብቻ! ኦ ጋብቻ! ከልብ የተጠላህ፣ በእጅ ብቻ ከውጪ የተያዝክ ምን ዓይነት የተረገምክ ነህ!” ኤ. ሂል

“ሰው ባገባ ማግስት በሰባት ዓመት ያረጃል” ቤከን

“ከጨቅጫቃ ሚስት ጋር በአንድ ቤት ከመኖር ይልቅ፥ በጣራ ማእዘን ላይ መኖር ይሻላል” (ምሳሌ 25፥24)

እግዚአብሐር ጋብቻን ጣፋጭ አድርጎ ይፍጠረው እንጂ በውስጡ ያለፈ ሁሉ ጣፋጭነቱን አያወራም። በጋብቻ ሕይወታቸው የተጎዱ፣ ከኑሮ ጓደኞቻቸው ጋር በማያቋርጥ ጦርነትና ትግል ውስጥ የሚኖሩ፥ መራራውን የጋብቻ ጽዋ የጠጡ አልፎ አልፎ የችግራቸው ሁሉ ዋና ምክንያት እግዚአብሐር ስለሚመስላቸው በእርሱ ላይ ቅሬታቸውን ያሰማሉ።

“መልካም ትዳር ስጠኝ ብዬ ለመንኩት እንጂ የምድር ሲኦል ውስጥ ክተተኝ አልኩት እንዴ!” በማለት ያማርራሉ። ብዙዎች ችግራቸውን አይናገሩ እንጂ፥ በማያቋርጥ የጦርነት ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ ጥቂቶች አይደሉም። “በትዳሬ ውስጥ ሰላም አጣሁ” ለሚሉ ሁሉ ለችግራቸው አቋራጭ መፍትሄ መስጠት ብንችል ኖሮ ምን ያህል ደስ ባለን ነበር። የብዙዎች ችግር ውስብስብ ያለና አስቸጋሪ ነው። ከዚህ ሌላ ብዙዎች በትዳራቸው ውስጥ ያለባቸውን ችግር ለማንም ገልጸው አይናገሩም። ስለማይናገሩም ጠቃሚ ምክርና ሃሳብ በጊዜው ማግኘት አይችሉም። ብዙዎች ችግራቸውን ገልጠው የማይናገሩበት ምክንያት ምን ይሆን?

1) “የክርስትያኖች ሁሉ ጋብቻ ከችግር ነጻ ነው” ብለው ስለሚያስቡ “ችግር አለብኝ” ቢሉ ሰዎች ክርስትያንነታቸውን ይጠራጠሩ ይሆናል ብለው ስለሚፈሩ ነው።

2) “በጋብቻዬ ችግር አለብኝ” ቢሉ፥ ባሉበት ሕብረተሰብ የሚሰጣችው ክብርና ግምት ይቀንስ ይሆናል ብለው በማሰብ ነው።

3) አሉባልታና ወሬ ስለሚፈሩ ነው።

4) የባህል ተጽእኖ-በባህላችን ችግርን መደበቅ የተለመደ በመሆኑ ነው።

5) ምክር የሚሰጡ ባለሞያዎች (Counselors) በብዛት በአገራችን ስለሌሉና ከአዋቂዎች ምክር ማግኘት የተለመደ ስላልሆነ ነው።

“በትዳሬ ውስጥ ሰላም አጣሁ” በማለት ጩኸታቸውን በአደባባይ በግልጽ ኢያሰሙት እንጂ በብዙዎች ሰዎች ቤተ የተለመደ ውስጣዊ የእሮሮ ድምጽ ነው። ጋብቻን የመሠረተ እግዚአብሔር ስለሆነ፥ አስፈላጊነቱና ጠቃሚኒቱ የሚያጠያይቅ አይሆንም። መሥራቹ እግዚአብሔር ባይህን ኖሮ ብዙዎች የዓለም ሰዎች እንደተናገሩት ገና ጥንት “የጋብቻ ተቋም” ሞቶ በተቀበረ ነበር። ጋብቻን ጣፋጭ ወይንም መራራ እንዲሆን የሚያደርጉት ወይንም ምክንያት የሚሆኑት ሰዎች ራሳቸው ናቸው። አንዳንድ ሰዎች እንደሚገምቱት ክርስትያን በመሆናችን ብቻ የጣፈጠ የጋብቻ ሕይወት ይኖረናል ማለት አይደለም። ወይንም መልካም የጋብቻ ሕይወት የሌላቸው ሰዎች መልካም ትዳር ካላቸው ሰዎች ያነሱ ክርስትያኖች በመሆናቸው አይደለም። ብዙዎች በትዳራቸው ሰላም እንዲያጡ ያደርጋቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ከነዚህ መካከል ጥቂቶቹ ለመጥቀስ እንሞክራለን።

## ጎጂ የሆነ የቃላት ልውውጥ

ብዙ ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ብዙ ጊዜ በቃላት ሲጎዳዱ ይታያሉ። ይህን ዓይነት ባህሪ የሚታየው አዲስ በተጋቡ ባልና ሚስት ላይ ብቻ ሳይሆን ለረጅም ዘመን በጋብቻ ላይ በቆዩትም ላይ ነው። ይህን የሚያደርጉት በቤታቸው ውስጥ ለተፈጠረው ችግር ምክንያት ሌላው ሰው ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው። እንዲሁም ሌላው ሃሳባቸውን የማይቀበል ከሆነ ያንን ሰው የሚቀጡበት የራሳቸው የሆነ የቃላት በትር አላቸው።

ካሰች ባላት የጋብቻ ሕይወት እርካታ ስለሌላት ብዙ ጊዜ “በትዳሬ ውስጥ ሰላም እንዲኖር ለምን አታደርግም?” በማለት በእግዚአብሔር ላይ ታማርራለች፤ በቤቷ ውስጥ ያለባትን ፈተና ለክርስትያን ጓደኞቿ  እንዲያዝኑላት ይሁን ወይንም ለሌላ ምክንያት ብዙ ስታወራ ትሰማለች። አንድ ቀን ጠዋት ካሰች ባሏን “አሁንስ ሰለቸኝ! ምን ዓይነት ጽዳት የማትወድ ዝርክርክ ሰው ነህ! በጤረጴዛውና በየወንበሩ ሥር ያንተን የሸተተ ካልሲና የውስጥ ሱሪ መለቃቀሙ ሰለቸኝ! እኔ እኮ ሚስትህ እንጂ ሰራተኛህ አይደለሁም። ዛሬ ጠዋት ስነሳ ሱሪህን መኝታ ቤት፣ ሸሚዝህን ከምግብ ጠረጴዛ ሥር፣ ጫማህን ሳሎን፣ ካልሲህን ባኞ ቤት ነው ያገኘሁት። ባኞ ቤቱማ አይወራ! ከታጠብክ በኋላ ምን አለ ገንዳውን ብታጥበው? ሰውነትህን ያደርቅህበትን ፎጣ መሬት ጥለኸዋል! እንደ አንተ ያለ ዝርክርክና ፈጽሞ ጽዳት የማይወድ ሰው በሕይወቴ አላየሁም!” ስትል ተናገረችው።

ሳምሶን የሚስቱ አነጋገር አበሳጭቶት ሚስቱን በተራው በምላስ ጅራፍ የሚገርፍበትን ያሰላስል ስለነበረ ምን ያህሉን እንደሰማት አይታወቅም። ቁና ቁና እየተነፈሰ በንዴት “እንደ አንተ ንጽህና የማያውድ ዝርክርክ ሰው የለም ነው ያልሽው? የራስሽን ዝርክርክነት ማን በነገረሽ! እስቲ ማቀዝቀዣውን ክፈቺና እይው! ወጥ ቤት ያሉትን ኮመዲኖዎች ሳብ ባደርግሁ ቁጥር አንዳንድ ነገር ተንጠባጥቦበት፣ ቅመሙ ፈስሶ ሳይ እዚህ ቤት ውስጥ ሴት አለበት ብዬ ማመን ያቅተኛል።

ባኞ ቤትስ ደግሞ ያንጠለጠልሻቸው ጨርቆች ምን ያህል ጊዜ እዚያ እንደሆኑ ታውቂያለ? እኔን ዝርክርክና ንጽህና የማትወድ ብለሽ ስትነቅፊኝ አታፍሪም?” አላት።

ይህን ዓይነቱ የቃላት ልውውጥ ትዳርን ሲገነባ፥ ባልና ሚስትን ሲያቀራርብ፣ ባልና ሚስት ያለባቸውን ችግር ሲያቃልል አላየንም። ብዙ ትዳሮችን ግን እንዳፈረሰ እናውቃለን። ብዙዎች “በትዳሬ ውስጥ ሰላም አጣሁ” የሚሉ ሰዎች ይህን የመሰለ የቃላት ጦርነት እርስ በርሳቸው በመለዋወጣቸው እንደሆነ የተገነዘቡት አይመስለንም። ስለ ችግሩ በመወያየትና መፍትሄ በመፈለግ ፈንታ አንዱ ሌላውን የሚነቅፍበት፥ “ተነቀፍኩ” የሚለው መልሶ የሚወጋበትን መንገድና ዘዴ ይፈልጋል። ይህን ዓይነቱ የቃላት ልውውጥ የትም አያደርስም። እስቲ ከላይ የጠቀስናቸውን ባልና ሚስት ማለትም ካሰችንና ሳምሶንን ሁኔታቸውን እንመርምር። ካሰች ስለ ባሏ የተናገረቻው ሁሉ እውነት ነው። የሳምሶን ችግር ብቻ ሳይሆን የብዙዎች ባሎች ችግር ነው። ካሰች ባሏ ያወለቀውን ልብስና ካሲ አንስቶ በቦታው እንዲያስቀምጥ በመንገር ፈንታ የነቀፋና የወቀሳ ቃላት መወርወር ባላስፈለጋትም ነበር። አቀራረቧ ወይንም አነጋገሯ ባሏን ሳምሶንን ስላስቆጣው በተራው የራሱን የቃላት ጦር እንዲወረውር አደረገው።

በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ሳምሶን “ለምን ተነካሁ? ለምን ተደፈረኩ?” በማለት ፈንታ ሚስቱ የእርሱን ልብስና ካልሲ በየወንበሩ ሥር መለቃቀሙ ምን ያህል እንደሰለቻት ተገንዝቦ ራሱን ልማረም ጥረት ማድረግ ይገባው ነበር። በአጠቃላይ በሁለቱም በኩል ችግራቸን ለማቃለል የሞከሩት አንዱ ሌላውን “በምላስ ጅራፍ” በመግረፍ ነው። ምላስ ክፉ ሰዎች ሌሎችን የሚጎዱበት መሣሪያ እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። “ክፉ ሰዎች ሌሎችን የሚጎዱበትን መንገድ ያስባሉ፤ ንግግራቸውም እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው” ይላል ምሳሌ 16፥27። ደጋግ ሰዎች ግን በምላሳቸው ማንንም አይጎዱም። “ደጋግ ሰዎች ከመናገራቸው በፊት ያስባሉ፤ አመጸኞች ግን በችኮላ ክፉ ቃል ይናገራሉ” (ምሳሌ 15፥28)። “ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ መናገር እጅግ ያስደስታል” ይላል ምሳሌ 15፥23። ባልና ሚስት ትዳራቸውን መራራ ከሚያደርግባቸው ምክንያቶች አንዱ ጤናማ ያልሆነ የቃላት ልውውጥ ስለሆነ አንዱ ሌላውን የሚያንጽበት በጎ ቃል ይለዋወጡ እንጂ አንዱ ሌላውን የሚያፈርስ ቃል አይለዋወጡ። “ያለ ጥንቃቄ የተነገረ ቃል እንደ ሰይፍ ያቆስላል፤ በጥበብ የተነገረ ቃል ግን ይፈውሳል” ይላል ምሳሌ 12፥18።

## ያለቦታው የሆነ ሙገሳና “እሹሩሩ” ባይነት

ትዳርን መራራ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አንደኛው ባልና ሚስት አንዱ በሌላው ላይ የሚወረውሩት የቃላት ጦርነት እንደሆነ ተመክተናል። የሚወረውሩት ቃላት ፍቅራቸውን ሲያቀዘቅዝ፥ ያላቸውን አንድነትና ህብረት ሲያራርቅ እንጂ አንዱ ሌላውን እንዲገነባ ሲያደርግ ትዳራቸውን ሲያለመልም አይታይም። የምላስን ጎጂነት የተረዱ አንዳንድ ባልና ሚስት ደግሞ በክፉ ንግግራቸው በመዋጋት ፈንታ እርስ በርሳቸው ሲሞጋገሱ ይሰማሉ። መሞጋገሱ ጥሩ ሲሆን ያለቦታውና ከመጠን ያለፈ ከሆነ ደግሞ ያንኑ ይህል ጎጂነት አለው። ኤፍሬም ሚስቱን ማን ያህልሻለን ቁንጅናዋን እያደነቀ መናገር ይወዳል። ሊጎበኙአቸው የሚመጡ አንዳንድ ወዳጆቻቸው ከነኤፍሬም ጋር ጥቂት ጊዜ አሳልፈው ሲሄዱ ሚስቶቻቸው “ሚስትን መያዝ እንደ ኤፍሬም ነው እንጂ” እያሉ በማድነቅ ለባሎቻቸው ሰላም የነሱ አልጠፉም።

ማን ያህልሻል ሳህን ለማጠብ ብድግ ያለች እንደሆነ፥ “ተይ! ጣቶችሽ ይበላሻሉ፤ እኔ አጥባለሁ” ሻይ ለማፍላት ከተነሳች “ተይ እሳቱ ያቃጥልሻል፤ የእኔ እመቤት እኔ አደርገዋለሁ” በማለት በቀላሉ እንደምትሰበር አሻንጉሊት አድርጎ ይመለከታታል። ኤፍሬም በዚህ ተግባሩ ማን ይህልሻን እንደ ሚስት ያለባትን ኃላፊነት እንዳትለማመድና ፍጹም በራሷ እንዳትቆም በማደረግ ደካማ ሴት አደረጋት። እርግጥ ነው ኤፍሬም ሚስቱን በጣም ይወዳታል፤ ይሁን እንጂ በአጉል ሙገሳውና እንክብካቤው ሰው በመሆን ፈንታ ተቀባብታ፣ አምራ የምትታይ አሻንጉሊት ብቻ እንድትሆን አደረጋት። በዚህ ምክንያት እያደር በሕይወቷ የምታዝንና የምትበሳጭ ሌላው ቀርቶ ለኤፍሬምም ለራሱ ሰላምን የምትነሳው ሴት ሆነች።

በጥሩ ንግግር አንዱ ሌላውን ማነጽ ጥሩ ነው። ባል ሚስቱ የምትሠራውን በጎ ነገር እያየ ለመልካም ሥራዋ ማመስገን እንደሚገባው መጽሀፍ ቅዱስ ይመክረዋል። “እርስዋ ለምትደርገው ነገር ሁሉ አመስግኑአት፤ ምክንያቱም ስለ መልካም ሥራዋ በሰዎች ሁሉ ዘንድ ልትከበር ይገባታል” (ምሳሌ 31፥31)። ይሁን እንጂ ትክክል ያልሆነውን ባህሪና አቋም ማሞገስ የተሞገሰውን ሰው ብቻ ሳይሆን፥ አሞጋሹንም ወደ ኋላ ሲጎዳ ይታያል። ስለዚህ ዛሬ የምናገረው ንግግር በሌላው ሰው ሕይወት ላይ ምን ያስከትላል? ይገነባል ወይንስ ያፈርሳል? ብለን መጠየቅ ይገባናል። መልካም ነው ብለን ያደርግነው ነገር ያልጠበቅነውን ዓይነት ውጤት ሲያስከትል “ምነው እንደዚያ አንቀባርሬ ይዣት…” በማለት ስናማርር እንሰማለን።

………………………………………………………………………